# መድልዎን የተመለከተ ቅሬታን ለሰብአዊ መብቶች አስከባሪ ቢሮ ማመልከት የሚቻልበት መንገድ

ሰኔ 2011

## መግቢያ

የሰብአዊ መብቶች አስከባሪ ቢሮ (Office for Civil Rights (OCR)) ከትምህርት ሚኒስቴር (Department of Education (ED) የፌደራል የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙ ፕሮግራሞችና ተግባራት በዘር፣ በቀለም፣ በብሔራዊ ማንነት፣ በጾታ፣ በአካል ጉዳተኝነት እና በዕድሜ ምክንያት አድልዎ እንዳያደርጉ የሚከለክሉ አምስት የፌዴራል ሰብዓዊ መብቶችን ተፈጻሚ ለማድረግ ይሠራል። በዘር፣ በቆዳ ቀለም እና በብሔራዊ ማንነት ላይ ተመርኩዞ መድልዎ መፈጸምን በ1964 የወጣው የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ (Civil Rights Act of 1964) 6ኛው አንቀጽ ይከለክላል፤ የጾታ መድልዎን በ1972 የወጣው የትምህርት ማሻሻያ ደንብ አንቀጽ 9 (Education Amendments of 1972) ይከለክላል፤ በአካል ጉዳተኝነት ላይ የተመሠረተ መድልዎን በ1973 የወጣው የተሃድሶ ድንጋጌ (Rehabilitation Act of 1973) ክፍል 504 እና የ1990ው አሜሪካውያን አካል ጉዳተኞችን የሚመለከተው ድንጋጌ (Americans with Disabilities Act of 1990) አንቀጽ 2 ይከለክላል (አንቀጽ 2 የፌዴራሉን የገንዘብ ድጋፍ ቢያገኙም ባያገኙም በሕዝባዊ ተቋማት የሚደርሰውን በአካል ጉዳተኝነት ላይ የተመሠረተ መድልዎን ይከለክላል)፤በ1975 የወጣው የዕድሜ መድልዎ ድንጋጌ (Age Discrimination Act of 1975) ደግሞ ዕድሜን መሠረት ያደረገ መድልዎን ይከለክላል።

እነዚህ የሰብአዊ መብት ሕጎች በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የፌዴራሉን የገንዘብ ድጋፍ በሚያገኙ መንግሥታዊ የትምህርት ቢሮዎች፣ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች፣ የሙያ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶች፣ የግል ትምህርት ቤቶች፣ የግዛቱ የተሐድሶ ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከሎች፣ አብያተ መጻሕፍት እና ቤተ-መዘክሮች ሁሉ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። በትምህርት ሚኒስቴሩ በኩል የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ፕሮግራሞችና ተግባራት ዕርዳታዎችን፣ ጥቅማጥቅሞችን ወይም አገልግሎቶችን ከመድልዎ በጠራ መንገድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። እዚህ ላይ የተጠቀሱት ዕርዳታዎች፣ ጥቅማጥቅሞች ወይም አገልግሎቶች ምዝገባዎችን፣ የሠራተኛ ቅጥርን፣ የገንዘብ ዕርዳታን፣ የቀለም ትምህርት መርሐ ግብሮችን፣ የተማሪዎችን አያያዝና አገልግሎቶችን፣ የምክር አገልግሎትና አመራር መስጠትን፣ ቅጣትን፣ የክፍል ሥራዎችን፣ ደረጃ መስጠትን፣ የሙያ ትምህርት መስጠትን፣ መዝናኛን፣ የአካል ማጎልመሻ ትምህርትን፣ አትሌቲክስን፣ የቤት ኪራይንና ሥራን የሚያካትቱ ሊሆኑ ቢችሉም በእነዚህ ብቻ የተወሰኑ አይደሉም።

በተጨማሪም OCR በአሜሪካ ቦይ ስካውቶች እኩል ተደራሽነት ድንጋጌ (Boy Scouts of America Equal Access Act) ስር የተካተተውን የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ድንጋጌን (Elementary and Secondary Education Act) ያስፈጽማል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት OCR በእኩል ተደራሽነትን የሚነፍግ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ መብት የማይሰጥ፣ ወይም መድልዎው በማንኛውም ቡድን ከቦይ ስካውቶቹ ጋር ሕጋዊ ስምምነት ያለው ቡድንም ይሁን በዩናይትድ ስቴትስ ሕግ አንቀጽ 36 ላይ ከተዘረዘሩት የወጣት ቡድኖች መካከል አንዱ፣ በሕዝብ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በሕዝብ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም ከትምህርት ዘርፉ የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኝ የመንግሥት ወይም የአካባቢው የትምህርት ቢሮ፣ የሚቀርቡትን ቅሬታዎች መመርመር ይችላል።

## የመድልዎ ቅሬታ ሊያቀርብ የሚችለው ማን ነው?

የፌዴራሉን የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኝ አንድ የትምህርት ተቋም በአንድ ሰው ላይ ዘሩን፣ የቆዳ ቀለሙን፣ ብሔሩን፣ ጾታውን፣ የአካል ጉዳተኝነቱን ወይም ዕድሜውን መሠረት ያደረገ መድልዎ ፈጽሟል ብሎ የሚያምን ማንኛውም ሰው፣ ወይም አንድ የሕዝብ የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወይም የመንግሥት ወይም የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ የአሜሪካ የቦይ ስካውቶች እኩል ተደራሽነት ድንጋጌን ተላልፏል ብሎ የሚያምን ሁሉ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል። ቅሬታውን የሚያቀርበው ሰው ወይም ድርጅት የግድ የተጠቀሰው መድልዎ ሰለባ መሆን አያስፈልገውም፤ ነገር ግን ሌላን ሰው ወይም የሰዎች ቡድን ወክሎ ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል።

## የጊዜ ገደብ

በአንዳንድ ሁኔታዎች ከሚታዩ አሳማኝ ምክንያቶች በመነሳት OCR ቅሬታ የማቅረቢያውን የጊዜ ገደብ ካላራዘመው በስተቀር ተፈጸመ የተባለው መድልዎ በተከሰተ በ180 ቀናት ውስጥ ቅሬታው መቅረብ ይኖርበታል።

## የተቋማዊ ቅሬታ አያያዝ ሥርዓት

አንድ ቅሬታ አቅራቢ በአንድ ተቋም ላይ የተሰማውን ቅሬታ ለOCR ከማቅረቡ በፊት ተቋሙ ቅሬታ የሚያስተናግድበት የአሠራር ሥርዓት እንዳለው አጣርቶ በተዘረጋው ሥርዓት በመጠቀም ቅሬታውን ሊፈታ ይገባል። ይሁን እንጂ ለOCR ቅሬታውን ከማቅረቡ በፊት ተቋሙ በዘረጋው የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት እንዲጠቀም ሕግ አያስገድደውም። አንድ ቅሬታ አቅራቢ በተቋሙ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓትም ተጠቅሞ እንደገና ለOCR ቅሬታውን ሊያቀርብ ቢፈልግ ቅሬታ አቅራቢው የተቋቋመውን የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት ተጠቅሞ ካበቃ በኋላ በሚኖሩት 60 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይኖርበታል።

የትምህርት ሚኒስቴር ተልእኮ የትምህርት ጥራትንና እኩል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በመጣር የተማሪዎችን ውጤት ማሳግና ለዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ማዘጋጀት ነው።

## ቅሬታ የሚቀርብበት መንገድ

ቅሬታቸውን ማቅረብ የሚፈልጉ ቅሬታ አቅራቢዎች ቀጥሎ የተጠቀሱትን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ፦

**በፖስታ ወይም በፋክስ መላክ፦** ቅሬታ አቅራቢዎች ደብዳቤያቸውን በፖስታ ወይም በፋክስ ሊልኩ ወይም ከOCR ሥራ አስፈጻሚ ቢሮዎች ከአንዱ (በዚህ ብሮሹር ላይ የተዘረዘሩትን የOCR ቢሮዎች ሊመለከቱ ይችላሉ) በ OCR የተዘጋጀውን የመድልዎ ቅሬታ ማመልከቻ ቅጽ መጠቀም ይችላሉ። በሚጽፉበት ጊዜ እባክዎ ደብዳቤዎ ከዚህ በታች የተገለጹትን ማካተቱን አይዘንጉ፦

•የቅሬታ አቅራቢው ስም፣ አድራሻ እና ከተቻለ (የግድ ባያስፈልግም) ቅሬታ አቅራቢው በሥራ ሰዓት ሊገኝ የሚችልበት የስልክ ቁጥር፤

•በመድልዎ አማካኝነት ጉዳት ስለደረሰበት ግለሰብ ወይም የሰዎች ቡድን የሚገልጽ መረጃ (ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ስም መጥቀስ አያስፈልግም)

•የተጠቀሰውን መድልዎ የፈጸመው ተቋም ስምና ቦታ

•OCR ምን እንደተፈጸመ፣ መቼ እንደተፈጸመ እንዲሁም ተፈጸመ ለተባለው መድልዎ ምክንያት የሆነውን ነገር (ዘር፣ የቆዳ ቀለም፣ የብሔር፣ የጾታ፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ የዕድሜ ወይም የአሜሪካ የቦይ ስካውቶች እኩል ተደራሽነት ድንጋጌ) በዝርዝር የሚያስረዳ

**ኢ-ሜይል፦** ቅሬታ አቅራቢዎች ቅሬታቸውን በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ተጠቅመው መላክ ይችላሉ፦ ocr@ed.gov። ከላይ እንዳለው ይጠቀሙ።

**ኢንተርኔት፦** ቅሬታ አቅራቢዎች ቅሬታቸውን OCR ለማቅረብ የOCRን የኤሌክትሮኒክ ቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ ለመሙላት በሚከተለው ድረ ገጽ መጠቀም ይችላሉ፦ http://www.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ወቅታዊ የሆነ የኢ-ሜል አድራሻ ለሌላቸው በአካባቢያቸው ከሚገኝ ቤተ መጻሕፍት ነጻ የኢንተርኔት አገልግሎት ማግኘት የሚቻል ሲሆን ከሌሎች ትላልቅ አገልግሎት ሰጪዎች ደግሞ ነጻ የኢ-ሜል አካውንት ማግኘት ይቻላል።

ማሳሰቢያ፦ የፌዴራሉን የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኝ ማንኛውም ተቋም በዚህ ብሮሹር የመጀመሪያ ገጽ ላይ በተዘረዘረው ሕግ መሠረት አንድ ጉዳይ እንዲመረመር ወይም እንዲጣራ ቅሬታ ባቀረበ፣ ምሥክር በሆነ፣ በተባበረ ወይም በተሳተፈ በማኛውም ግለሰብ ላይ የበቀል እርምጃ መውሰድ አይኖርበትም። ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በአንዱ የተነሳ በቀል እንተፈጸመብዎ የሚያምኑ ከሆነ ቅሬታዎን ለOCR ማቅረብ ይችላሉ።

**U.S. Department of Education**
Arne Duncan
*Secretary*

ሰኔ 2011

# ቢሮዎችና አድራሻዎች

## ዋና መሥሪያ ቤቶች

U.S. Department of Education
Office for Civil Rights
400 Maryland Ave. SW
Washington, DC 20202-1100
Customer Service: 800-421-3481
Fax: 202-453-6012
TDD: 877-521-2172*
E-mail: OCR@ed.gov
Web: http:www.ed.gov/ocr

**Connecticut, Maine, Massachusetts, New Hampshire, Rhode Island, Vermont**
Office for Civil Rights, *Boston Office*
U.S. Department of Education
5 Post Office Square, 8th Floor
Boston, MA 02109-3921
Telephone: 617-289-0111*
Fax: 617-289-0150
E-mail: OCR.Boston@ed.gov

**New Jersey, New York, Puerto Rico, Virgin Islands**
Office for Civil Rights, *New York Office*
U.S. Department of Education
32 Old Slip, 26th Floor
New York, NY 10005-2500
Telephone: 646-428-3800*
Fax: 646-428-3843
E-mail: OCR.NewYork@ed.gov

**Delaware, Maryland, Kentucky, Pennsylvania, West Virginia**
Office for Civil Rights, *Philadelphia Office*
U.S. Department of Education
100 Penn Square East, Suite 515
Philadelphia, PA 19107-3323
Telephone: 215-656-8541*
Fax: 215-656-8605
E-mail: OCR.Philadelphia@ed.gov

**Alabama, Florida, Georgia, Tennessee**
Office for Civil Rights, *Atlanta Office*
U.S. Department of Education
61 Forsyth St. SW, Suite 19T70 Atlanta, GA 30303-8927
Telephone: 404-974-9406*
Fax: 404-974-9471
E-mail: OCR.Atlanta@ed.gov

**Arkansas, Louisiana, Mississippi, Texas**
Office for Civil Rights, *Dallas Office*
U.S. Department of Education
1999 Bryan St., Suite 1620
Dallas, Texas 75201-6810
Telephone: 214-661-9600*
Fax:: 214-661-9587
E-mail: OCR.Dallas@ed.gov

**North Carolina, South Carolina, Virginia, Washington, D.C.**
Office for Civil Rights, *District of Columbia Office*
*U.S. Department of Education 400 Maryland Ave. SW Washington, DC 20202-1475*
*Telephone: 202-453-6020* Fax: 202-453-6021*
*E-mail: OCR.DC@ed.gov*

**Illinois, Indiana, Minnesota, Wisconsin, Iowa, North Dakota**
Office for Civil Rights, *Chicago Office*
U.S. Department of Education
Citigroup Center
500 W. Madison St., Suite 1475
Chicago, IL 60661-7204
Telephone: 312-730-1560*
Fax: 312-730-1576
E-mail: OCR.Chicago@ed.gov

**Michigan, Ohio**
Office for Civil Rights, *Cleveland Office*
U.S. Department of Education
1350 Euclid Avenue, Suite 325
Cleveland, OH 44115
Telephone: 216-522-4970*
Fax: 216-522-2573
E-mail: OCR.Cleveland@ed.gov

**Kansas, Missouri, Nebraska, South Dakota, Oklahoma**
Office for Civil Rights, *Kansas City Office*
U.S. Department of Education
One Petticoat Lane
1010 Walnut Street, Suite 320, 3rd Floor
Kansas City, MO 64106
Telephone: 816-268-0550*
FAX: 816-268-0599
E-mail: OCR.KansasCity@ed.gov

**Arizona, Colorado, New Mexico, Utah, Wyoming**
Office for Civil Rights, *Denver Office*
U.S. Department of Education
Cesar E. Chavez Memorial Building 1244 Speer Blvd., Suite 310
Denver, CO 80204-3582
Telephone: 303-844-5695*
Fax: 303-844-4303
E-mail: OCR.Denver@ed.gov

**California**
Office for Civil Rights, *San Francisco Office* U.S. Department of Education
50 United Nations Plaza
San Francisco, CA 94102
Telephone: 415-486-5555*
Fax: 415-486-5570
E-mail: OCR.SanFrancisco@ed.gov

**Alaska, Hawaii, Idaho, Nevada, Oregon, Washington, American Samoa, Guam, Northern Mariana Islands, Montana**
Office for Civil Rights, *Seattle Office*
U.S. Department of Education
915 Second Ave., Room 3310
Seattle, WA 98174-1099
Telephone: 206-607-1600
TDD: 206-607-1647
Fax: 206-607-1601
E-mail: OCR.Seattle@ed.gov